*ረቡዕ ሰኔ 11 ቀን 2000 ዓ.ም. (June 18, 2008) ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ሊቀመንበር ተደርጋ ከተመረጠች በኋላ ለመሥራች ጠቅላላ ጉባዔው ያደረገችው ንግግር*

**የተከበራችሁ የአንድነት ለዴሞክራሲ እና**
**ለፍትህ ፓርቲ ጠቅላላ ጉባዔ አባላት፣**
**ጥሪ የተደረገላችሁ እንግዶች ክቡራት**
**እና ክቡራን**

ከሁሉ አስቀድሜ በአገራችን መንግሥታዊ ሥርዓት የሕዝብ የሥልጣን ባለቤትነትን ለማረጋገጥ ሲደረግ በቆየው የትግል ሂደት ከገጠመን አይነተ ብዙ ፈተና በኋላ ለዛሬዋ ታሪካዊ ቀን በመድረሳችን ሁላችንም እንኳን ደስ ያለን እላለሁ::

ለዚህ ጠቅላላ ጉባዔ ስኬትም በትጋት ሲሰሩ የቆዩትን የፓርቲውን አስተባባሪ ኮሚቴ አባላት እና የሌሎች ዘርፍ ኮሚቴዎች አባላት በዚህ አጋጣሚ ላመሰግናቸው እወዳለሁ::

በተጨማሪም ይህ ታላቅ ጉባዔ እንዲሁም ጉባዔው የአቋቋመው ብሔራዊ ምክር ቤት ባደረጉአቸው ነጻ እና ዴሞክራሲያዊ ምርጫዎች ብሩህ ነገን ለኢትዮጲያ የፀነሰን ታላቅ አላማ ወደ ፍፃሜው ለማፍጠን ለሚደረገው የፖለቲካ ትግል አመራር ለመስጠት እምነት ጥላችሁብን ስለመረጣችሁን በራሴ እና  በተቋቋመው የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ሥም ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ::

**ክቡራት እና ክቡራን**

**ዛሬ ሚሊዮኖች በቃላቸው ብቻ ሳይሆን በምርጫ ካርዳቸውም ጭምር ለተሻለ የፖለቲካ ሥርዓት፣ ለኢኮኖሚያዊ ብልጽግና እና ለዜጎች ነፃነት መከበር የሾሙትን የቀንጅትን ዓላማ እና መንፈስ ከገባበት ሥርጓጉጥ ውስጥ ነጥቆ አውጥቶ በአዲስ ኃይል ይዞት ሊገሰግስ የተነሳውን ወደ ኢትዮጵያ የፖለቲካ አየር አንድነት በሚል ስያሜ መምጣቱ ዛሬ የተበሰረውን አንድነት ለዴሞክራሲ እና ለፍትህ ፓርቲን በሊቀመንበርነት እንድመራ ስትመርጡኝ የተሰማኝ ስሜት ዕጅግ የላቀ ነው::**

ለዛሬዋ የአንድነት ፓርቲ ሊቀመንበር ህይወትን ለሕዝብ አገልግሎት መስጠት መስዋዕትነት አይደለም፡፡ የከበረ የዜጋ ተግባር እንጂ፡፡ በሁለንተናችን ያዋረደንን ድህነት፣ እንደ ዜጋ የተነፈግነውን የሰው ልጅ ክብር እና ነፃነት፣ የሚገባችሁ ይህ ነው የተባልነውን ኢ-ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት፣ በሥልጣን ለመክረም ሲባል ብቻ በግራ ቀኝ የተጎነተለውን የሕዝብ አንድነት ሳይለምዱ እና ሳይቀበሉ ከውድቀታችን ስለምንነሳበት፣ ከውርደታችን ስለምንወጣበት ስለመንገዱ ማሰብ፤ አስቦም መተለም፣ ተልሞም መቀመር መተግበር ለእኔ ከብዙ የኑሮ ጎዳናዎች ውስጥ እንደ አንዱ ከሚወሰድ አማራጭ በላይ ነው፡፡

ስለዚህም ከእነ ውጣ ውረዱ፣ ከእነ ተግዳሮቱ ታላቅ ለሆነው ለዚህ ተልዕኮ ሕይወቴን የማውልበት ከፍ ያለ እድል ስለሰጣችሁኝ የጉባዔውን እንዲሁም የብሔራዊ ምክር ቤታችንን አባላት ከልብ አመሰግናለሁ፡፡ በዚህ አጋጣሚም ይህን የተሰጠኝን ሃላፊነት በፍጹም ታማኝነት፣ በግልጽነት፣ በተጠያቂነት እና በጋራ አመራር መርህ በፍጹም ቁርጠኝነት ለጉባዔው ቃል ልገባ እወዳለሁ፡፡

ይህ የዛሬ ምርጫ ግን ከዚህም የዘለለ መልእክት በውስጡ አዝሏል ብዬ አምናለሁ፡፡ ይህ ጉባዔ እኔን የ34 ዓመት ወጣት ሴት የፓርቲ ሊቀመንበር አድርጎ ሲመርጥ በድምፁ ብዙ ቁምነገሮችን ተናግሯል፡፡ ይህም የአገራችንን ጠቅላላ የፖለቲካ ሂደት የፖለቲካ ባህል እና አሠራርን ከመለወጥ አንጻር ከፍተኛ ፋይዳ እንደሚኖረው አንዳች ጥርጥር የለኝም፡፡

እንደ አገር ያለንበት አሳዛኝ እና አሳፋሪ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚአዊ እና ማኅበራዊ ሁኔታ የለውጥ በስፋት በጥልቀት እንዲሁም በፍጥነት መምጣትን የሚጠይቅ ነው፡፡ ፖለቲካችንን ነጥለን ወስደን ዛሬ የምንገኝበት የዜጎች መሠረታዊ መብቶች ዋስትና ያጡበት፣ የፖለቲካ ተቃውሞ መተንፈሻ ስፍራዎች ያለ አግባብ የጠበቡበት፣ መንግሥት የሕዝብ ተጠያቂ ሳይሆን ሕዝብ ለመንግሥት ተጠያቂ የሆነበት ሥርአት ስረ ምክንያቱን ስንመረምር የመነሻ ነጥቡ 1983 ዓ.ም የችግሩ ሁሉ አድራጊ ፈጣሪም ኢህአዴግ ብለን ብንደመድም የሃቀኝነትን ሚዛን ከማዛባት ውጪ ሌላ ምንም ሊባል አይቻልም፡፡

እንደ አገር ያለንን የፖለቲካ ባህል የተጠናወተው የዜሮ ድምር ጨዋታ፣ በአዎንታዊ ፉክክር ላይ ሳይሆን  በጠላታዊነት መንፈስ የሚመራው የፖለቲካ ተዋስኦ እና ንግግር፣ የመቻቻል እጦት፣ ኢ-ዴሞክራሲያዊነት፣ ፀረ ግልጽነት እና የመሳሰሉት በየሥርዓቱ ያቆርናቸው፣ በየዘመኑ ያዳጎስናቸው፣ በሁላችን ቤት እንደየመጠኑ ራሳቸውን የሚገልጡ የድሪቷችን መገለጫዎች ናቸው::

አጠቃላይ የፖለቲካ ሂደቱን ከዚህ ጉተታ ካላላቀቅነው፣ ድሪቶውን ካልቀደድንለት፣ አዲስ ፈር ካልቀየድንለት ኢህአዴግ ከሥልጣን ቢሰናበት እንኳን እውነት ለመናገር አንዳች ከሚያክለው አቀበት የምንወጣው ጋቱን ብቻ ይሆናል::

የተከበራችሁ የፓርቲያአችን መስራች ጉባዔ አባላት ፍጹም ግልፅነትን የተላበሰ የአባላትን ተሳትፎ በሁሉም ደረጃ የአረጋገጠ የተለያዩ ነጻ ሃሳቦች መንሸራሸሪያ ብሎም የተሻሉ የፖሊሲ አማራጮች መፍለቂያ የሆነ ጠንካራ እና ዘመናዊ ፓርቲ እንዲኖረን ካስፈለገ ለውጥ በሁሉም መስክ ለውጥ ከምር ያስፈልጋል::

ይህ ሂደት የተለመዱ የዴሞክራሲ መርሆዎችን ከማነብነብ ያልፋል:: የእያንዳንዱን አባል ራሱን በእነዚህ እምነቶች ማነጽ፣ ራሱን መለወጥ ከዛም አልፎ እያንዳንዱን የፓርቲ እንቅስቃሴ ከዚህ አንጻር ማደስን፣ በአጠቃላይ መስተጋብሩም በዚሁ መልክ መጫወትን ይጠይቃል::

ይህን መሰል ሁሉን አቀፍ፣ ሁሉን አጣቃሽ ለውጥ ለማምጣት ደግሞ ከማንኛውም የኅብረተሰብ ክፍል በላይ በስሜቱ ለለውጥ ቅርብ የሆነው ለለውጡ ለሚያስፈልገው እንቅስቃሴም ኃይል እና ጉልበት ለመስጠት የሚችለው የወጣቱ ትውልድ ወደ መድረኩ መምጣት መጥቶም ባለ ሚና መሆን አስፈላጊ እና የግድ ነው::

እንደ እኔ እምነት ዛሬ ፓርቲአችን ለውጥን መርጧል፤ ለውጥንም አጠናክሮ ለመቀጠል ወስኗል:: ወጣቱን ትውልድም ለፖለቲካ ተሳትፎ ለአገራዊ ኃላፊነት ጋብዟል፤ ተመጣጣኙን አዎንታዊ ምላሽ እንደሚያገኝም ጽኑ እምነቴ ነው::

**ክቡራን የጉባዔ ተሳታፊዎች**

**ክቡራን ጥሪ የተደረገላችሁ እንግዶች**

**ክቡራት እና ክቡራን**

በኢትዮጵያ በገዢም ሆነ በተቃውሞ ፖለቲካ ከሕዝባችን ብዛት ገሚሱን የሚሸፍኑት ሴቶች ያላቸውን ድርሻ እና ስፍራ ስንመለከት እዚህ ግባ የማይሰኝ መሆኑ ማንም የማይክደው ሃቅ ነው:: ዴሞክራሲ ከምንም በላይ ስለተሳትፎ በመሆኑ የአንድ አገር ሴት እና ወንድ ዜጎች በእኩልነት ላይ በተመሰረተ አጋርነት የፖለቲካውን መሪ እስካልዘወሩት ነጻነቱም ነፃነት ዴሞክራሲውም ዴሞክራሲ የመሆኑ ነገር ፈጽሞ አይታሰብም:: በርግጥ የአገራችን የመንግሥት ሥርዓት የዴሞክራሲያዊነት መመዘኛዎች ሁሉ በማያወላዳ መልኩ የወደቀ መሆኑ ይታወቃል::

በዚህ የተበላሸ መልክ ምትክ የዜጎችን ክብር እና ነፃነት የአረጋገጠ፣ የሥልጣን ምንጭ ሕዝብ ስለመሆኑ በተግባር የሚታይበት፣ የፖለቲካ ልዩነቶች ሁሉ በጠረጴዛ ዙሪያ ከዚያም ሲያልፍ በሕዝብ የድምፅ ፍርድ እልባት የሚያገኙበትን የፖለቲካ ሥርዓት ለመትከል ከተነሳን በሂደቱም ሆነ በመዳረሻው ሴቶች የጉዳዩ ባለቤቶች እና ተዋናዮች ሊሆኑ የግድ ነው::

**<u>ክቡራት የአንድነት መሥራች ጉባዔ አባላት</u>**

እናንተ ዛሬ ከፓርቲው የኃላፊነት ሥፍራ የመጀመሪያውን ሴት በሆነች ሰው እንዲያዝ ወስናችኋል:: በዚህም በኢትዮጵያ የሚመስለው ሌላ ቀዳሚ ኩነት የሌለው ታሪክ ሰርታችኋል፤ ሴቶች የወንድሞቻቸው እህቶች፣ የአባቶቻቸው ልጆች፣ የባሎቻቸው ሚስቶች ብቻ ሳይሆኑ በማኅበረሰብ የለውጥ ሂደት ውስጥ እኩያ አጋሮች፤ አስተዋጽኦቸውም እንደ ወንዶቹ ሀሉ አስፈላጊ እና ምትክ የለሽ መሆኑን አውጃችሁ አል::ፓርቲያችንንም የከፍተኛ ለውጥ ፋና ወጊ አድርጋችሁታል:: ለዚህ አኩሪ ተግባር የሶስት ዓመት ሕጻን ልጄን ሀሌይን ጨምሮ ከ 40 ሚሊየን በላይ የኢትዮጵያ ሴት ዜጎች ስም፣ እንዲሁም በየቦታው የተረሱ የኢሕአዴግ ታጋዮችን ጨምሮ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክ የሚችሉትን ለመከወን በሞከሩ ሴቶች ስም ሁሉ ለዚህ ጉባዔ ከፍተኛ ምስጋናዬን ላቀርብ እወዳለሁ::

**ክቡራት እና ክቡራን**

የዛሬው አንድነት ለዴሞክራሲ እና ለፍትህን በወለደው በቀድሞው ቅንጅት ጥላ ስር ተሰባስበን በመራነው እና ባለፍንበት የፖለቲካ ትግል እንደ ድርጅት፣ እንደ እንቅስቃሴ፣ እንዲሁም እንደ ግለሰብ የአይነት ብዙ ጥቃት ሰለባዎች ሆነናል:: ይህ ጥቃት ግን ከውጭ የተሰነዘረ ብቻ አልነበረም:: በአጭሩ የትግል ታሪካችን እንደ ትግሉ መልክ ተወስደው የነበሩ የአመራር አባላቶቻችን ሳይቀሩ የጎጆአችንን ዋልታ ማገር ሊነቀንቁት ሞክረዋል:: ከተቀናቃኞቻችን ጡጫ ይልቅ የጓዶቻችን አዳካሚ ተግባር የለውጥ ተስፋውን በጫርነው ኀብረተሰብ ዘንድ ሃዘን እና ተስፋ መቁረጥን መፍጠሩ የሚካድ አይደለም::

በዚህ ሂደት የድርጅቱን እንቅስቃሴ የማስተባበር ሚና ሲጫወት እንደነበረ መሪ ዛሬ አንድ ነገር ላረገግጥላችሁ እወዳለሁ፤ ከቀድሞው ፓርቲ መሪዎች ከእሥር መፈታት በኋላ ያለፍንበት እያንዳንዱ አታካች ሂደት የወደፊቱን የድርጅታችንን ማንነት የተደላደለ መሠረት የሚያረጋግጡ ወሳኝ ትምህርቶችን ሰጥቶን አልፏል::

በዚህም የተነሳ የፈረሰው ለመፍረሱ፣ የወደቀው ለመውደቁ፣ የደበዘዘው ለፍዘቱ ሥረ ምክንያቱን ለማየት ያስቻለንን ሂደት ለጊዜው በትግሉ እንቅስቃሴ ላይ አሉታዊ ውጤት ቢኖረውም፤ ዛሬ ለጀመርነው አዲስ የለውጥ ምእራፍ መንደርደሪያ፣ ከቀድሞ በላቀ ታላቅነት ለመነሳት የሚያገለግለን መስፈንጠሪያ ስፕሪንግ ቦርዳችን በመሆኑ ፓርቲውን እንዳጋጠመ ውስብስብ ችግር ብቻ ሳይሆን እንደ ታላቅ የለውጥ አጋጣሚ ሊወሰድ ይገባል እላለሁ:: በዚህ ውጣ ውረድ አብረን ለሕግ የበላይነት እና ለዴሞክራሲያዊ አሠራር ለመገዛት የቆረጡ የፓርቲአችንን ቤተሰቦች በሙሉ አጠጋግተን ሚሊዮኖች በመረጡት፣ ብዙዎች ህይወታቸውን ሳይቀር በሰዉለት ዓላማ ዙሪያ ተሰባስበን ለዛሬ ከበቃን ቀጣዩ ተግባር እነዚህን በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የቀሰምናቸውን ትምህርቶች በአግባቡ ተገንዝበን ወደፊት መገስገስ ብቻ ይሆናል::

ዛሬ ከተመረጠው የፓርቲ አመራርም ድርጅቱ ከዚህ በኋላ በሚኖረው የፓለቲካ ትግል ጉዞ በሁኔታዎች ወዲህ ወዲህ የሚወስድ ሳይሆን ከወዲሁ በተቀመረ ስትራቴጂ

በዝርዝር በታወቁ ታክቲኮች የፓርቲው ሠላማዊ ትግል እንቅስቃሴ ወደ ግቡ እየገፋ መሆኑን ማረጋገጥ ይጠበቅበታል፡፡

## የድርጅታችን የጠቅላላ ጉባዔ አባላት

## ክቡራት እና ክቡራን

ለድርጅቱ የወደፊት እጣፈንታ ጋር ተያይዞ የማይታለፍ አንድ አሳሳቢ ጉዳይ አለ፡፡ እርሱም አንድነትም ሆነ በአገሪቷ ውስጥ በሰላማዊ መንገድ የሚንቀሳቀሱ ተቃዋሚ ፓርቲዎች የምንንቀሳቀስበት የፖለቲካ ስፍራ እለት ተዕለት እየተበላሸ እለት ተዕለት እየጠበበ መምጣቱ ነው፡፡ አቶ መለስ እና መንግሥታቸው በ1997 ዓ.ም. አንድ የስሌት ስንተት ፈጽመዋል፤ የፖለቲካ ሥፍራው በተወሰነ ደረጃ ቢለቀቀም ተቃዋሚዎች እዚህ ግባ የሚባል ተቀባይነት አያገኙም የሚል፡፡በአንጻራዊነት ውድድሩ ውድድር፣ ምርጫውም ምርጫ ሲሆን ግን ውጤቱ ያለው መልክ ተቃራኒውን በማሳየቱ በሥልጣን ርካብ እስከ ዝንተ ዓለም ለመቆየት ያሰቡ በሚመስል ሁኔታ በ1997 ዓ.ም. ከተከተሉት ስልት ፍጹም ተቃራኒውን ለመከተል ወስነዋል፡፡ ለዚህም የፖለቲካ ፓርቲዎች በነፃነት የመደራጀትን ለመገደብ የተደነገገው ሕግ፣ የሲቪል ሶሳይቲ አደረጃጀትን ከቀጨጨው በላይ ለማቀጨጭ የረቀቀው አዋጅ፣ ለፕሬሱ የተፈጠረው አሸማቃቂ ድባብ ወዘተ ጉልህ ማሳያዎች ይኾናሉ፡፡ ከዚህ በመነሳት እየተጠየቀ የሚገኘው ጥያቄ ሠላማዊ ትግል በእንዲህ አይነት ከባቢያዊ ሁኔታ ውስጥ ስኬታማ ሊሆን ይችላል ወይ የሚለው ነው፡፡

በእኔ እምነት የፖለቲካ ስፍራውን ገዢው አካል በሚችለው መጠን ሊዘጋው ቢሞክርም የትግሉ ዋነኛ ባለቤት እና አንቀሳቃሽ የሆነው ሕዝብ ባልረታም መንፈስ በጽናት እስከቆመ የየአንዳንዱ ሠላማዊ ታጋይ ልብ በሠላማዊ እምቢ ባይነት እስከረጋ ድረስ ሁሌም ለሠላማዊ ትግል ተስፋ አለ፡፡ የፖለቲካ ሥፍራው በር ዋናው ቁልፍ ወይም ማስተር ኪይም የሚገኘው በገዢው ዘንድ ሳይሆን በሠላማዊው ታጋዩ እጅ ነው፡፡ ገዢው ራሱን ባለ በሌለ ጉልበቱ ሲያንሰራፋ በሕግም ያለ ሕግም የማያዋጣ ጥንካሬ ለራሱ ሲሰጥ፣ ያለ ኔ ማን ብሎ የፖለቲካ አየሩን ሙሉ በሙሉ ሊሞላው ሲንጠራራ የሠላማዊ ታጋዩ ልብ የፈሰሰ ዕለት፣ የሠላማዊ ትግል ታዳሚው ቁልፉ በእጁ መኖሩን ረስቶ ተስፋ የቆረጠ ዕለት በርግጥ ያን ቀን በሩ ላይከፈት ተከርችሟል፡፡

የተከበራችሁ የጉባዔ አባላት በዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ እያንዳንዱ ዜጋ ለሕንጻው ምሉዕነት እጅግ አስፈላጊ እንደሆነ የሸክላ ጡብ ነው:: የዚህ ሕንጻ አንድ የመዓዘን ድንጋይ መቻቻል ሌላው የሰው ልጅ ነፃነት፤ ሌላው ደግሞ ሠላም ይባላል:: እነዚህን ቀለሞች በላዩ ያልያዘ ሸክላ ደግሞ ፈጽሞ የዚህ ግንባታ አካል ሊሆን አይችልም፡

## ወገኖቼ

በረጅሙ የሰው ልጅ የፖለቲካ ታሪክ ሂደት ውስጥ ሁላችንን እንደሚያገናኝ ናፍቆት የታየው የነፃነት ፍላጎት በአገራችን የገሃድ መገለጫ፣ የሥርዓት ማረጋገጫ እንዲኖረው እስከፈለግን ከግባችን ለመድረስ እስከወደድን ሰፊውን የኅብረተሰብ ክፍል ያስተሳሰረ፣ ያስተባበረ እና ያሳተፈ የማኀበረሰብ እንቅስቃሴ መፍጠር፣ በሰው ልጅ የተፈጥሮአዊ መብቶች ሰላማዊ ትግበራ በሚመነጭ ጉልበት የሚተማመን የሠላማዊ ትግል ሠራዊት ማሰለፍ የግድ ነው:: በአሰልቺው እና በአስቸጋሪው ነገር ግን ውጤታማነቱ አስተማማኝ በሆነው በዚህ ሂደትም ይህ ሠራዊት ራሱን፣ ማኀበረሰቡን እንዲሁም መንግሥትን ይለውጣል:: የድሉ ብቻ ሳይሆን የትግሉም ባለቤት በመሆን ህዝብ ሥልጣን ባለቤት ለመሆኑ የራሱ ዋስትና ያበጃል:: በመጨረሻም መሠረቱ የማይነቃነቅ ሕዝባዊ ሥልጣን የተረጋገጠበት ሥርዓት ከመገንባት ማንም አምባገነን አያግደውም:: ስለዚህም በፓርቲያችን አዲስ ምዕራፍ ጅማሬ ላይ ቆሜ በሠላማዊ ትግል የተቃኘውን ከፊታችን የተዘረጋውን ጎዳና ሳስብ  የኣላማችን ስኬት እንዲህ እናንተን እንደማያችሁ ወለል ብሎ ይታየኛል:: መንገዱ ትንሽ ረዘም ይል ይሆናል፤ ቁልቁለት አቀበትም ሳይበዛውም አይቀርም፤ ሌላ አቋራጭ ግን የለም::

**የተከበራችሁ የጉባኤ አባላት**

ዛሬ በአዲስ ምዕራፍ ላይ ቆመናል፤ ትግሉ ስለትናነት ሳይሆን ስለ ነገ፣ ስለ ስጋታችን ይሆን ሥለተስፋችን፣ ስለድካማችን ሳይሆን ስለምንፈጥረው ብርታት ነውና የዛሬውን አጋጣሚ በመጠቀም የጉባኤውን አባላት በሙሉ ባልታጠፈ ግንባር በጸና

ቁርጭምጭሚት በታጠቀ ወገብ በአንድነት ለሠላማዊ ትግሉ በአዲስ ኃይል እንትመም በአንድነት እያልኩ ጥሪዬን አቀርባለሁ።

***አመሰግናለሁ!!!***